## ገቢር አራት

አጎት አሊ

ዋናው ገፀ-ባሕርይ <ግራንድ ሌይ> ወይም አያት ሌይ ሲሆን የበለጠ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ለመግባባት <አጎት አሊ> ተብሏል::

በትረካ የሚሰማ

- በጠዋት እናቴ የአጎቴ አሊን በጠና መታመም ነግራኛለች!
- በዚህም ምክንያት እርሱና አክስቴ ፋጢማ በከተማው መሃል ያለውን መኖሪያ ቤታቸውን በመተው ለኑሮ ወደ እኛ መጥተዋል::
- ይህ ለምን እንደተከሠተ አልገባኝም

አሊ - እሺ ወዳጄ ...... አስቂኝ ነው

- (በትረካ መልክ የሚቀርብ ነው)
- ቀናት አለፉ ነገር ግን እስከ አሁን አጎቴ ምን እንደሆነ አላውቅም
- ጥያቄዎቼን ማንም አልመለሰልኝም እናቴም ብትሆን!
- ምናልባት ትንሽ ልጅ ስለሆንኩ አይረዳም ብለው ገምተውኝ ይሆናል
- ከቀን ወደ ቀን የአጎቴ ሁኔታ እየባሰ ሄደ አንድ ምሽት ላይ . . .

(ከሌላ ክፍል)

አክስት ፋጢማ - ፍጠኑ ፍጠኑ! አሊ ራሱን ስቷል! አሁኑኑ ወደ ክሊኒክ መውሰድ ይኖርብናል፡፡ ቶሎ በሉ

ኺየክ - አክስቴ! እውነት አጎቴ በጣም ታሟል::ግን ይኼ ክሊኒክ ያድነዋል?

አክስት ፋጢማ - ኺየክ አጎትህ የኤድስ ሕመምተኛ ነው::

ኺየክ - አጎቴ እንደዚህ ታሞ ለምን ቤታችሁን ለቃችሁ ወጣችሁ?

አክስት ፋጢማ - የቤቱ ባለቤት ቤቱን ለቃችሁ ውጡ ስላለንና ሌሎቹ ነዋሪዎችም የአጎትህን ሁዔታ ያውቃሉ:: እንደውም በበሽታው እንያዛለን ብለው በጣም ፈርተው ነበር::

ኺየክ - የአጎቴ በሽታ በአደገኛ ሁኔታ የሚተላለፍ ከሆነ ለምን ሁላችንም አልተያዝንም በተለይም እኔ! የሱን ምግብ እበላ ነበር::

(በትረካ መልክ የሚቀርብ)

- በዚህ ሁኔታ ነበር ለእኔ የኤድስ እውነትነት የታወቀኝ
- ይህን በሽታ በቴሌቪዥን ብቻ ነበር የማውቀው አሁን ግን በእውነት አየሁት::

- ዶ/ር ሲላ - አቡሽ ነገሩ ግልጽ ነው::
- የአጎትህ ጎረቤቶች የሆኑት ሰዎች የተሟሟተ መረጃ ነበር ያገኙት ይኸው ነው!
- ታውቃለህ ጾታዊ ግንኙነትን የተመለከተ ውይይት ለወላጆች የሚከብድ ነው:: ለእነርሱ ብቻ ሳይሆን ለአንዳንድ ዶክተሮችም ጭምር::
- ተመልከት የኤድስ ቫይረስ ዋና መተላለፊያው የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ነው
- የአጎትህ ጎረቤቶችም ሆኑ አንተ ከደም ንክኪ ከራቃችሁ በፍፁም ምንም አደጋ አያገኛችሁም::
- አንድ ሰው ምንም እንኳ ኤድስ ቢኖርበትም በተመሳሳይ ኩባያ መጠጣት በአንድ ሰሃን መብላት እንዲሁም ያለፍርሃት መተቃቀፍ ይቻላል::

ኂየክ - ዶክተር! አጎቴን መርዳት እችላለሁ?

ዶ/ር ሲላ - አጎትህን ትወደዋለህ አይደል?

- ምን ያህል እንደምትንከባከበው አስቲ አሳየው
- ይኸውልህ መድኃኒት የታዘዘበት ወረቀት
- እነዚህን መድሃኒቶች ለአጎትህ በቀን ለበርካታ ግዜያት (እንዲታዘዘው) እንድትሰጠው እፈልጋለሁ . . . እነዚህ መድኃኒቶች በጣም ጠንካራ እና በእውነት ውጤት የሚያመጡ ናቸው:: እሺ ::

ኂየክ - <ከእርሱ ጎን መቆም! ማክበር! መውደድ>

አሊ - ደህና ዋልክ . . .

ኂየክ - አጎቴ እንዴት ነህ ?

አሊ - ስላንተ እያሰብኩ ነው. . .

- ስላንተ በጣም እየተጨነቅሁ ነው :: . . .
- ጆሮዎችህ ልዩ ናቸው በጣም እንግዳ . . .
- የሚያምታቱ/በእጁ የያዘውን ከረሜላ ይሰጠዋል/

*******